በደም የታጠበች ህይወት

ትዕይንት ፩

ኢዮብ፡- አንተ ልጅ ተው ይሄ ልጅ ያበላሽሃል። ተው ከሱ ጋር አቁም። ከሱ ጋር ጓደኝነት ጥሩ አይመጣም።

ፍፁም፡- የትኛው ልጅ? ገረመው? ኖ በፍፁም አያበላሸኝም።

ማርታ፡- ተው ፍፁሜ ተው እሱ ልጅ ጥሩ ስነ ምግባር የለውም።

ሁሉም ባንድነት፡- ተዉት በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ሁሌ እነግረዋለሁ እመክረዋለሁ የራሱ ጉዳይ። በለው ተንጫጭቶው ይቆጡታል።

ፍፁም፡- የመናደድ ባህሪ ያሳይና በመጨረሻም ጥሏቸው ይወጣል። እነሱም በመገረም ያጉረመርማሉ። መጋረጃው ይዘጋል።

ትዕይንት ፪

ገረመው፡- መጋረጃው ሲከፈት ብቻውን ቁጭ ብሎ ሲያስብ ይታያል። ፍፁሜም ይመጣለታል።

ፍፁሜ፡- ገረመው ብቻውን ተቀምጦ ስለ ነበር አንኳኩቶ ይገባል። ሰላምታ ይጠያየቃሉ።

ገረመው፡- ቤቱ ደስ አይልም ፍፁሜ ለኑሮ? ለእኔ እና ላንተ ይህቺ ቤት የኑሮ መሰረት ልትሆነት ትችላለች።

ፍፁሜ፡- ምን ለማለት ፈልገህ ነው? እኔ ቤተሰቦቼን እንዴት አድርጌ ትቼ ነው ባከህ ካንተ ጋር የምሆነው?

ገረመው፡- ሾሽሽሽ... ብሎ ይስቅና
እስከ ዛሬ ባለ ማወቅህ
ባጣም ታሳዝናለህ በሞኝነትህ
የማርታ አባት አንተን ለጉልበትህ ሲሉ ነው ያሳደጉህ።
አንተ... አባትህ እሱ እንደሆነ ታውቃለህ?
እነሱን እህቶቼና ወንድሞቼ ብለህ ታምናለህ?
እጅግ በጣም ሞኝ ሰው በመሆንህ

ፍፁም፡- ታዲያ ድሮስ ትጠራጠር ነበር ወንድማቸው መሆኔን?
አባቴስ መሆኑን እስከ ዛሬ አታውቅምን?
<u>ቆይ</u> ይልና፡- ግን... ምን እያወራህ ነው? ነው ወይስ የምትናገረውን አታውቅም?

ገረመው፡- ባውቅማ ነው የምነግርህ
እሱም... ልጃቸው ያለመሆንህ።

ፍፁሜ፡- እየተጨነቀና ብቻውን እያወራ እየተበሳጨ ሲወጣ መጋረጃው ይዘጋል።

ትዕይንት ፫

መጋረጃ ሲከፈት የፍፁም እባት/አቶ ሐይሉ/ እቤት ቁጭ ብለው ቦርሳቸውን በመከፈት እያነበቡ ሳለ ፍፁም ይገባል።

አቶ ሐይሉ፡- ልጄ ምሳህን በልተሃል ወይስ እንዴት ነው?
ማርታ ምሳህን ትስጥህ?
ፊት ፊቱን ለጥቂት ጊዜ አየት፣ አየት ያደርጉና ምነው ታዲያ የተጨነቅህ ትመስላለህ? ምን ሆነህ ነው?
ወይስ ከእዮብ ጋር ተጣላህ ማለት ነው? እባከህ ልጄ ጭንቀትህን ንገረኝ።

ፍፁሜ፡- እቤት ገብቶ ከአባቱ ጋር ሆኖ አባቱ ለሚጠይቁት ጥያቄ እሱ ይጨነቅ ስለ ነበር በቂ መልስ አይሰጥም። ይመነጫጨቃል።
<u>ልጁ</u>... ማ... እኔ ያንተ ልጅ ነኝ?

አቶ ሐይሉ፡- ታዲያስ ፍፁሜ ትጠራጠራለህ?

ፍፁም፡- በቃህ አባባ አትደብቀኝ
ታሪኩን ሳታስቀር ዘርዝረህ ንገረኝ

አቶ ሐይሉ፡- ምን አይነት ታሪክ ነው የምነግርህ
<u>ወይኔ ሐይሉ</u>። ምን አይነት ጉዳይ ገጠመኝ? ይላሉ ጠጨንቀው
ፍፁሜ ልጄ ነህ። ለምን ትጠራጠረኛለህ!?

ፍፁም፡- አይደለሁም አባባ። ለምን ትዋሸኛለህ? እኔ ማን ነኝ? ለምን ትደብቀኛለህ? እየጮኸ እየተቆጣ ይናገራል።

አቶ ሐይሉ፡- ትንሽ ይረጋጉና አዎ ፍፁሜ እስከ መቼ እደብቅሃለሁ? ታሪኩም እንደዚህ ነው።

የነማርታ እናት ደስታ
በሆስፒታል ተኝታ
በጣም የሚያለቅስና የሚያሳዝን ልጅ በምሬት
የማን ልጅ ነው? ብለን ጠየቅነው አስተናጋጁን በድፍረት
የልጁንም ሁኔታ ብንጠይቀው
እናትየው ወልዳ ከሆስፒታል መጥፋቷን አወቅነው

አይኢ ያቺ ቀንማ እርጉም ነች
የልጆቹ እናት ደስታም አንቀላፋች። ሞተች። እያሉ እየተንሰራደዱ ያለቅሳሉ።

ፍፁም፡- ይህን ሁሉ ጉድ ማርታና እዮብ ያውቁታል?

አቶ ሐይሉ፡- አዎ ያውቁታል። እስቲ አሁን ልሄድ ስለሆነ ማርታና እዮብን ጥራልኝና ና በአይናቸው አየት ያደርግና ቤቃ ተወው ፍፁሜ አየመጡ ነው። እቤት የገቡት ልጆቻም ሰላምታ ያቀርባሉ እዮብና ማርታ

ማርታ፡- አባዬ ትኬት ቆርጠንልሃል። በደንብ ተዘጋጅተሃል?

አቶ ሐይሉ፡- ፍፁሜ ሂድና በሻንጣ ልብሱን ከተህ እዚህ አምጣልኝ።

ፍፁሜ፡- አላመጣም አባዬ። አንተ እኔን ብቻ ነው የምትልከው?

አቶ ሐይሉ፡- ተወው በቃ እዮብ ያምጣልኝ። እዮብም ያመጣለታል። ሌሎቹ ሲሸኙት ፍፁም ግን ቅር ያለው ይመስላል። ፊቱንም እንደ ከሰከሰ የግዱን ተጎትቶ አብሮ ሲወጣ መጋረጃው ይዘጋል።

ትዕይንት ፬

መጋረጃው ሲከፈት ፍፁሜ ከገረመው ቤት አብረው ተቀምጠው ሲነጋገሩ ይታያል።

ፍፁሜ፡- እውነትህን ነው ያልከው ገረመው፣
የፈለጉኝ እኔን ለጉልበቴ ሲሉ ነው።

ገረመው፡- አሁን ገና ትንሽ ትንሽ መደመር እንደቻለ ህፃን ማሰብ ጀምረሃል። አዎ ተረዳኸው አይደል? ንብረታቸውንም ተካፋይ ልትሆን አትችልም።

ፍፁም፡- ስለዚህ ምን ማድረግ ይሻላል ገሬ?

ገረመው፡- ስለዚህማ አባትዬውን ወደ ላይኛው አለም ማሸጋገር ነዋ።

ፍፁም፡- ማንን? አባዬን?

ገረመው፡- ታዲያ ምን ማድረግ ትችላለህ?

ፍፁም፡- ገሬ ይሄማ... የአርዮስነት ስራ ነው።

ገረመው፡- ያለህ አማራጭ ይህ ብቻ ነው።

ፍፁም፡- ካልከማ አመቺ ነው።
አባዬ ቼኩን ሊያመጣ ወደ ባንክ ቤት ሄዷል።

ገረመው፡- እንዲህማ ከሆነ ቆንጆ አጋጣሚ ሆኗል።
የሚመጣው መቼ እንደሆነ አውቀኸዋል?

ፍፁም፡- ዛሬ ማታ እንደሚመጣ እርግጠኛ ሆኛለሁ።

ገረመው፡- በቃ ማታ ጠብቀን ቼኩን እንረከበዋለን።
ተያይዘውም በፍጥነት ትጥቃቸውን ይዘው እየሮጡ ሄዱ። በተመካከሩት መሰረት አባትየውን ቀምተው ገደሉ።

አገዳደሉ፡- ፍፁሜ ሽጉጥ ደግኖበት ገረመው ቼኩን ሲቀበለው ነዱ ኪሱ ገብቶ ሲወስድ
-ወዲያ ፍፁሜ በያዘው ሽጉጥ አባቱን ገደለው።

ገረመው፡- ፍፁሜ/3/ ሽጉጡን/3/ ብለው ይሮጣሉ። መጋረጃውም ይዘጋል።

ትዕይንት ፭

ማርታ፡- ማርታም በጣም ተከዛ ጥቁር ለብሳ ተንበርክካ አዛኝቷ እመቤቴ አትርሽኝ የሚለውን መዝሙር እየዘመረች መጋረጃው ይከፈታል።

ገረመው፡- ፍፁሜና ገረመው በጣም አምሮባቸው ወደ ማርታ ይሄዳሉ። ማርታ ያባትሽን ገዳዮች ለመበቀል ዝግጁ ነን። ይላል ገረመው።

ማርታ፡- አትሳሳት የአባቴን ገዳዮች የሚበቀለው እግዚአብሔር ነው።

ፍፁም፡- ማርታ እዮብስ ወዴት ሄደ?

ማርታ፡- የአባቴን ገዳዮች እበቀላለሁ ብሎ ሄደ።

ፍፁም፡- እግዚአብሔር ይርዳሽ ብለው ከገረመው ጋር ጥለዋት ይወጣሉ። እሷም ኩርምት ብላ ቁጭ ትላለች። መጋረጃውም ይዘጋል።

ትዕይንት ፮

መጋረጃ ሲከፈት ፍራሽ አንጥፉ ማርታ ጥቁር እንደለበሰች 2 ሴት ልጆች አስተዛዝነዋት ይወጣሉ። ወዲያው ጌቱ የሚባለው ጓደኛዋ ብቻውን ይመጣል። ሰላም ብሏት እንዳበቃ ያፅናናታል።

ጌቱ፡- አባትሽ አረፉ የተባለ እለት ማታ ኢዮብ ጋር ነበር አመጣጤ። ፍፁሜ ሸጉጡን/3/ የሚል ድምፅና ወደዚያ ዞር ስል ደግሞ ይህችን ያንንት ሐብል አገኘሁ ይልና ያሳያታል።

ማርታ፡- የኢዮብ ጓደኛ ከነገራት በኋላ ሐብሉን ደጋግማ ታይና፡- ይህችን ሐብል ለፍፁሜ ሰጥቼው ነበር። በቃ የአባቴን ገዳዮች አውቂያቸዋለሁ። ፍፁሜና ገረመው ናቸው። ብላ ስቅስቅ ብላ ታለቅሳለች።

ጌቱ፡- /የጎደለ ወይም የሚጨመር አለ ስለማይነበብ አልተፃፈም/ የባሰ ህይወት ወደ ማጥፋትና ሐረመኔነት ስሚሰማሩ እግዚአብሔር ደማቸውን በከንቱ እንዳይጥል እየፀለይን ባንነግራቸውስ? ሲላት

ማርታ፡- እሺ በቃ አንናገርም /ብለው ተሳማምተው እሱ ወጥቶ ይሄዳል/ እነ ገረመውና ፍፁሜ ደግሞ በእግሩ ተተክተው ይገባሉ። እንደ ነገሩ ሰላም ተባብለው ያልፋሉ። ማርታንም ሰላም ይሏታል። ለሰላምታቸው ምላሽ ከሰጠች በኋላ

ፍፁሜ ያኔ የሰጠሁህን ሐብል የት አደረስካት?

ፍፁሜ፡- ደንግጦ ልቡን ያዝ ያዝ ካደረገ በኋላ፡- ኧ. ኧ. እቤት ነች።

ማርታ፡- ይህቺ ታዲያ ከየት መጣች። ብላ ሐብሉን አውጥታ ስታሳየው ደንግጦ ገረመውን አይን አይኑን ያየዋል።

ገረመው፡- ያባትሽን ገዳይ አላወቅሽም ?

ማርታ፡- ትሰማላችሁ «አንድ ሰው በጣም የምታምር እርግብ ነበረችው ይህቺ እርግብ በአንገቷ ወርቅ ነበራት።» ታዲያ ለዚህ አይነቱ ሰው ምን ይገባዋል?

ፍፁም፡- ይህንንማ መግደል ነዋ። ይላል እየተወራጨ።

ማርታ፡- በራስህ ላይ ፈረድክ ወንድሜ። /ብላ እቅፍ አርጋው ታለቅሳለች/

ፍፁም፡- ማርታ፣ ማርታ፣ በናትሽ ለማንም አትናገሪብን። በናትሽ ቃል ግቢልን?

ገረመው፡- በናትሽ እስከ ዛሬ ያፈራነውን ንብረት እናካፍልሻለን። እባክሽ ስለምታምኚበት ታቦት ብለሽ እባክሽ ተለመኚን።

ማርታ፡- አባዬ እንደሆነ አይመለስም። የሰውን ሐጢያት ብገልፅ አምላኬ ሐጢያቴን ይገልጥብኛል። እሺ ትቼዋለሁ። ትላለች።

ከቤት ወጣ ብለውም፡-

ገረመው፡- ማርታ በደንብ የነቃች ይመስልሃል?

ፍፁም፡- አይመስለኝም። ረጋ ባለ ድምፅ

ገረመው፡- የወንድማችሁ ጓደኛ የነገራት አይመስልህም?

ፍፁም፡- አይመስለኝም።

ገረመው፡- ምድነው ይመስልሃል አይመስልህም በአንዱ ሃሳብ አትረጋም። ብሎ እየተመናጨቀ ይናገራል።

ፍፁም፡- ታዲያ ምን ላድርግ። ሁሉ ነገር መምሰል ነው እንጂ መሆን ሆኖ አይታየኝም።

ገረመው፡- ምን ለማለት ፈልገህ ነው?

ፍፁም፡- ለምሳሌ ክርስትናን መምሰል እንጂ መሆንን አናውቅም።

ገረመው፡- ይህንንማ የሚያስበው ህሊና ያለው ሰው ነው።

ፍፁም፡- አንተ ህሊና የለህም?

ገረመው፡- ህሊናማ ቢኖረኝ ኖሮ እንደዚህ ባላደረኩ ነበር። አንተም ይሄኔ ህሊና አለኝ ትል ይሆናል። ሌላውም እንዳንተ ህሊና አለኝ ይል ይሆናል በሞኝነት አይሰው። በል ና እንሂድ ተባብለው እንደገና ቆም ይልና፡- በቃ ያለን አማራጭ ማርታንም ወደ አባቷ መላክ ነው።

ፍፁም፡- ማንን ማርትዬን በፍፁም ሊሆን አይችልም። ይላል በቁጣ

ገረመው፡- ታዲያ ምን እናድርግ? የዘረፍነውን ሳንበላ ወደ ዘብጥያ መውረዳችን እኮነው።

ፍፁም፡- ቆም ብሎ ያስብና ቆይ ለማርታ የነገራት ማን እንደሆነ ደርሼበታለሁ። እርሱም የኢዮብና የራሷ የማርታ ጓደኛ ጌቱ ሳይሆን እንዳልቀረ ይገባኛል።

ገረመው፡- በቃ ለመኖር መፍጨርጨር

ያለ መውደቅ መንገዳገድ

ወንዙን ከዳር ቆሞ ማሳለፍ

ፍፁም፡- so/ሶ/

ገረመው፡- ሐጢያትን ለመሸፈን አሁንም አሁንም ሐጢያት መስራት። ስለዚህ ጌቱ የምትለውን ልጅ መግደል። እርሷን ደግሞ የሄዋን ዘር እንደመሆኗ ማታለል። ብለው ተያይው ሲሔዱ መጋረጃው ይዘጋል።

ትዕይንት ፯

መጋረጃው ሲከፈት የነማርታ ጓደኛ ጌቱ እየፀለየ ነበር። ገረመው እና ፍፁም
የመግደያ ትጥቃቸውን አሟልተው ተሽሎክልከው መጥተው በጭለማ ቤቱን በርግደው ገቡ።
ሲፀልይ የነበረውን ጌቱን አፍጥጠው ተመለከቱት

ፍፁም፡- ሽጉጡን መተኮስ አቅቶት ይንቀጠቀጣል።
ገረመው፡- ቀጥቃጣ ፈሪ ፈርፋራ ብሎ ሽጉጡን ተቀብሎ ይገለዋል። ተያይዘውም በጭለማ ሲሮጡ መጋረጃው ይዘጋል።

ትዕይንት ፭

መጋረጃ ሲከፈት ፖሊስ ጣቢያ መሆኑ ነው። ሻለቃው ቁጭ ብሎ ሲያዝ ፖሊሱ ግን በመቆም ምላሽ ይሰጣል።

ሻለቃው፡- የአቶ ሐይሉን ገዳዮች ደርሰህባቸዋል?
ፖሊስ፡- አዎ። ሰሞኑን ኢንፎርሜሽን ስሰበስብ ነበር። በቅርቡ መኪና ሊያስጣ መሆኑን ደርሼበታለሁ። ይህንንም የሚገዛው ከአቶ ሐይሉ በዘረፈው ብር ነው።
ሻለቃው፡- ማነው ማለት ነው።
ፖሊስ፡- ገረመው መሆኑን በቂ መረጃ አለኝ።
ሻለቃው፡- በሉ አሁኑኑ እዚህ ድረስ አምጡልኝ። ተሰናብቶ ሰላምታ ሰጥቶ ይሄዳል። መጋረጃ ይዘጋል።

ትዕይንት ፮

መጋረጃ ሲከፈት ፍፁም ገረመው ቤት ቁጭ ብሏል።
ገረመው፡- ፍፁሜ መኪና ላስመጣ ተነጋግሬአለሁ 150,000 ሺ ብር የተነጋገርኩት ላሁን ነው። ስለዚህ ቼኩን ብትሰጠኝ።
ፍፁም፡- ለምን? ገረመው በጣም ትቸኩላለህ። በዚህ ላይ ደግሞ ፖሊሱ በጣም እየፈለገን ነው።
ገረመው፡- ምንም ችግር የለውም አምጣ ። ቼኩን ብትሰጠኝ ይሻልሃል።
ፍፁም፡- አላመጣም። ብዙ ይጨቃጨቃሉ።
ገረመው፡- ብታመጣ ይሻልሃል። ብዙ ይጨቃጨቃሉ። ትዕግስቱም ሲያልቅ ሰላም ያልወደደ ሃይል ይገዛዋል። ብሎ ሽጉጡን ያወጣል። ባንድ እጁ ቢራውን እየጠጣ።
ፍፁም፡- /የሆነ ነገር ይናገራል ስለ ማይማይነበብ አልተፃፈም/
እየጮኸና እየተቆጣ ይህን ካለ በኋላ ቼኩን ወርውሮለት ወጥቶ ይሄዳል።
ገረመው፡- በአለማችን ላይ በጣት የሚቆጠሩ አርዮሶች አሉ። ከነዚያም እኔ አንዱ ሳልሆን አልቀርም። ኧ. ኸ. ኸ. ይስቃል ቢራውን ብቻውን እየተነነጨ።
ቼኩ በእጇ ሲገባ ያሰብኩት ሲሳካ ምንኛ ደስ ይላል። ኧ. ኸ. ኸ. እያለ ሲስቅ በር ይንኳኳል።
ይግቡ ማን ነው? /ብሎ ሽጉጡን መሳቢያው ውስጥ ያስቀምጣል።
ፖሊስ፡- ቢተባበሩን እርስዎንና ቤቱን ብንፈትሽ? 2 ፖሊሶች ሆነዋል።
ገረመው፡- ምን አለ ታዲያ ወንደ ላጤ ነኝ። እያለ እየተወተወተ ቼኩ ጠረጴዛ ላይ ነበር። ወርውሮ በእግሩ ይቆምበታል።
ፖሊስ፡- የጠረጴዛውን ኪስ ሳብ አድርጎ አየህ አቶ ሐይሉ የሞቱበት ሽጉጥ ይሔ ነው። ይላል ላንዱ ፖሊስ
ገረመው የቆመበትን ቼክ ለማግኘት በል እግርህን አንሳ ይለዋል። እግሩንም ሲያነሳ ቼኩ ይገኝበታል። ከዚያ በኋላ እያዳፉ በሩን ዘግተው ይዘውት ይሄዳሉ። መጋረጃውም ይዘጋል።

ትዕይንት ፯

መጋረጃ ሲከፈት ኢዮብና ማርታ መድረክ ላይ ይታያሉ። ማርታ ተንበርክካ ሽጉጥ
ተደግኖባት።

ኢዮብ፡- ማርታ፡- ያባቴን ገዳዮች ታውቂያለሽ ምነው ብትነግሪኝ
ማርታ፡- ባትነግሪኝ የአባቴ አጥንት እሾሆ ሆኖ ይውጋሽ።
ልትናገር እየፈለገች ፍፁም እየፈራ እየተሳቀቀ ይገባል።
<u>ኢዮብ</u> ፍፁሜን፡- አትጠጋኝ/3/ ተበላሻለህ። ይላል።
ፍፁም፡- ቆይ/2/ አንዴ የምነግርህ ነገር አለ። ከተናገርኩ በኋላ ትገለኛለህ። /አባቱን መግሉ ይናገራል/
ኢዮብ፡- አንተ ነህ? አላምንም... /ብሎ ሳያስበው ደንግጦ ተኩሶ ይመታዋል። ከዚያን በኋላ ሽጉጡን ጥሎ እጇን በጇ እያለ አቅፎት ይጮሃል። ማርታም ከተንበረከከችበት ተነስታ አብራው ትጮሃለች።
ፍፁም፡- እግዚአብሔር ሆይ ማረኝ። ይቅር በለኝ። በለማወቄ አባቴን ገደልኩ። ይጨማምርበታል። /ሲናገር የነበረው በሽጉጥ ተመቶና እያቃሰተ ነበር/ ፍፁሜ ንስሀ ገብቶ ይሞታል። ኢዮብ በድንጋጤ ይጮሃል።

ተፈፀመ